
በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ



ከኖቬምበር 1-10/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ እና

ከኖቬምበር 11-20፣ 21-30/2026 የሚኖረዉ የአየር ሁኔታ

ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ


ኖቬምበር 2026

አዲስ አበባ

1. እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አስር ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት በደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች እንዲሁም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ ምስራቅና ሰሜን ምስራቅ ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን ነበራቸዉ። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በደቡብ፣ ምስራቅ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል። በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በ11 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1)።


በተጨማሪም በደቡብ ምዕራብና ደቡብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 39.0-68.4 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል። ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች ደብረ ሲና 68.4፣ ማሻ 60፣ ሞሯ 49.8፣ ሊሙጎነት 47፣ አፅቢ 44.1፣ አደሌ 40 ሚ.ሜ ይገኙበታል።




ምስል1: ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2026 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት የቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ፣ እና ምስራቅ ባሌ ዞኖች፤ ከሶማሌ ክልል የዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ ዶሎ፣ ነጎብ፣ እና ጃረር ዞኖች፤ የጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፤ ሁሉም የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ እንዲሁም የክረምት ወቅት ዝናብ ተጠቃሚ ከሆኑ ዞኖች ምዕራብ ወለጋ፣ የቄለም ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ ዞኖች፤ የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፤ የአኝዋክ፣ መኾርንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ ጎጃም እና የአዊ ዞኖች፤ የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ የወላይታ፣ ጎፋ እና ጌድዮ ዞኖች ላይ ከ5-80 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ1-5 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)። በተጨማሪም የሰሜን፣ መካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ ምስራቅ ጎጃም፤ የምዕራብ ሐረርጌ ዞኖች፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ እና ባሌ ዞኖች፤ የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ እና የመካከለኛ ትግራይ ዞኖች፤ ቅልበቲ፣ ፋንቲ፣ ማሂ፣ ሃሪ፣ ጋቢ ዞኖች ከ5-20 ሚ.ሜ የሚደርስ ወቅቱን ያልጠበቀ አነስተኛ መጠን ዝናብ ከ1-3 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)።


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት የቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ እና ምስራቅ ባሌ ዞኖች፤ ከሶማሌ ክልል የዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ ዶሎ፣ ነጎብ፣ እና ጃረር ዞኖች፤ የጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፤ ሁሉም የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ እንዲሁም የክረምት ወቅት ዝናብ ተጠቃሚ ከሆኑ ዞኖች የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ ዞኖች፣ የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፤ የአኝዋክ፣ መኾርንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ ጎጃም እና የአዊ ዞኖች፤ የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤የወላይታ፣ ጎፋ እና ጌድዮ ዞኖች ላይ በአብዛኛዉ ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ እና በጥቂት ቦታዎቻቸዉ ላይ ከመደበኛ በታች የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3)።



ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2026 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2026 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2026 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

1.2 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባለፉት አስር ቀናት በደቡብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ እንዲሁም ሰሜን፣ ሰሜን ምስራቅ እና አልፎ አልፎ በመካከለኛው የሃገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው እርጥበት ሙሉ ለሙሉ እድገታቸውን ላልጨረሱ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለፍርፍሬ ተክሎችና ለጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም በመኸር ወቅት መጨረሻ ላይ በአፈር ውስጥ በተከማቸ እርጥበት በመታገዝ ለሚዘሩ እንደ ጓያ እና ሽንብራ ለመሳሰሉ የጥራጥሬ ሰብሎች ጠቀሜታ ነበረው። በአንጻሩም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ የነበረው እርጥበት በተለይም በተወሰኑ በደቡብ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ለተዘሩ ሰብሎች ምቹ ሁኔታ የፈጠረ ሲሆን በአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሮች አካባቢ ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻልና የዝናብ ውሃን ለመሰብሰብና ለማከማችት ገንቢ ሚና ነበረው። በሌላም በኩል አልፎ አልፎ ሰብል በደረሰባቸው በሰሜን፣ በሰሜን ምስራቅ እና በመካከለኛው የሃገሪቱ ስፍራዎች የነበረው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በመጠኑም ቢሆን አሉታዊ ተፅእኖ ነበረው (ካርታ 4)።

1.3 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2026 የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስር ቀናት በአብዛኛው ኦሞ ጊቤ፣ ባሮ አኮቦ፣ መካከለኛና ላይኛው አባይ እንዲሁም የስምጥ ሸለቆ ተፋሰስ የተወሰኑ አካባቢዎች ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት አግኝተዋል፡፡ በተለይም በመካከለኛውና ታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ ላይኛው ባሮ አኮቦ እና በመካከለኛው አባይ ከፍተኛ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት የነበራቸው፡፡ በመሆኑም ይህ ሁኔታ የአፈር እርጥበትና የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት እንዲጠናከር እንዲሁም ለገፀ ምድር ውሃ ሀብት ግብዓት ጥሩ አስተዋፅየ እንዳደረገ የተተነተኑ የሀይድሮ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡ ፡ በተጨማሪም በላይኛው ተከዜ፣ በመካከለኛው አዋሽ እና በላይኛው አባይ የተወሰኑ አካባቢዎች ከቀላል እስከ መጠነኛ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት የነበረ ሲሆን፣ ይህም ለአካባቢያዊ የውሃ ሁኔታ መሻሻል አስገኝቷል (ካርታ 5)።




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

2.1 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በሚቀጥሉት የኖቬምበር የሁለተኛዉ አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በተለይም በመጀመሪያዎቹ አምስት ቀናቶች ላይ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት አከባቢዎች ላይ ይልበልጥ እንደሚጠናከሩ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም የቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ እና ምስራቅ ባሌ ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ሁሉም ዞኖች፣ የሶማሌ ክልል ደቡባዊና ደቡብ ምስራቅ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ላይ በመጠንም እና በስርጭት የተሻለ ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6)፡፡ በተጨማሪም በፀሀይ ሀይል ታግዘው ከሚጠናከሩት የደመና ክምችቶች ላይ በመነሳት በደቡብ፣ ደቡብ ምስራቅ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በ24 ሰዓት ውስጥ ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ የሚደርስ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል (ካርታ 6)፡፡ በሌላ በኩል አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት የምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ መካከለኛዉ፣ ምስራቅ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ወቅቱን ያልጠበቀ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6)፡፡ ስለሆነም በሚኖሩት ደረቅ ቀናቶች የደረሱ ሰብሎች መሰብሰብ አስፈላጊ መሆኑን የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ይጠቁማል፡፡ በሌላ በኩል በመካከለኛዉ፣ ምሥራቅ እና የደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ የለሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ከአምስት (5) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 7)፡



ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11-20/2026 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11-20/2026 የሚኖረዉ ዝቀተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን


በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች		
ክልል	ዞን	በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናብ መጠን
አሮሚያ	የቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ እና ምስራቅ ባሌ	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ)
ሶማሌ	የዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ ዶሎ እና ነጎብ፣ ጀረር፣ ዞኖች	መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ)
ደቡብ ኢትዮጵያ	ጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ)
ሲዳማ ክልል	ሁሉም የክልሉ ዞኖች	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ)
ወቅቱን ያልጠበቀ ቀላል መጠን ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎች		
አሮሚያ	ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ኢሊአባቦራ፣ ጅማ ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ የሰሜን እና የምዕራብ የሸዋ ዞኖች፣ ባሌ እና ዞኖች	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ)
አማራ	የሰሜን፣ የመካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ የምስራቅ፣ ሰሜን፣ ምዕራብ ጎጃም፣ የዋግ ህምራ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ የሰሜን እና ደቡብ ወሎ ዞኖች፣ የባህርዳር ዙሪያ እና የአዊ ዞኖች	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ)
ቤንሻንጉል ጉምዝ	የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች	ቀላል መጠን ያለው ዝናብ (ከ 1-10 ሚ.ሜ)
ጋምቤላ	የአኝዋክ፣ መኸርንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ)

ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ	የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ)
ደቡብ ኢትዮጵያ	የወላይታ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ ዞኖች	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ)
ትግራይ	የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ)
ሶማሌ	የሲቲ፣ ፋፈን እና ኤረር ዞኖች	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ)
አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ		ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ)
ሲዳማ፣ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ		ቀላል መጠን ያለው ዝናብ (ከ 1-10 ሚ.ሜ)

1.1 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21 እስከ 30/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመጪወቹ የኖቬምበር የሶስተኛዉ አስር ቀናት ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በጋ ሁለተኛ የዝና ወቅታቸዉ በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ ስርጭት እንደሚኖራቸዉ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የቦረና የምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ የሶማሌ ክልል ደቡባዊና ደቡብ ምስራቅ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ላይ ቀጣይነት ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም በፀሀይ ሀይል ታግዘው ከሚጠናከሩት የደመና ክምችቶች ላይ በመነሳት በደቡብ፣ ደቡብ ምስራቅ እና ደቡብ ምዕራብ፣ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በ24 ሰዓት ውስጥ ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ የሚደርስ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል (ካርታ 8)፡፡ በሌላ በኩል ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ

አካባቢዎች ወቅቱን ያልጠበቀ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በሌላ በኩል በመካከለኛዉ፣ ምሥራቅ እና የደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን ከአምስት (5) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች እንደሚሆንና፤ ከዚሁ ጋር በተያያዘም የለሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት እንደሚጠናከር የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ።



ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21-30/2026, የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

1.2 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ቀናት በደቡብ፣ ደቡብ ምስራቅ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገራችን አካባቢዎች በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ የአፈር ውስጥ እርጥበት እንደሚኖር ይጠበቃል። እንዲሁም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ፣ ምስራቅ ባሌ፣ የሲዳማ ክልል ሁሉም ዞኖች፤ የሶማሌ ክልል ደቡባዊና ደቡብ ምስራቅ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ላይ የተሻለ የአፈር ዉስጥ እርጥበት ያገኛሉ። እንድሁም አልፎ አልፎ በምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ሰሜን

ምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ ምስራቅ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ወቅቱን ያልጠበቀ አነስተኛ መጠን ያለዉ እርጥበት ይኖራል። በመሆኑም የሚኖሩ መልካም አጋጣሚዎችን በአግባቡ ለመጠቀምና አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ለመቀነስ የሚያስችል ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳብ ከወዲሁ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ከታች የቀረቡትን ዝርዝር ተግባራት ማከናወን ያስፈልጋል (ሠንጠረዥ 2)።

1.3 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሀ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ቀናት በላይኛውና መካከለኛው ባሮ አኮቦ፣ አሞ ጊቤ፣ መካከለኛውና ታችኛው ስምጥ ሸለቆ እንዲሁም ታችኛው ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ መካከለኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት ይጠበቃል። በታችኛው አሞ ጊቤ፣ በስምጥ ሸለቆ፣ በአባይ እንዲሁም ላይኛው አዋሽ ተፋሰሶች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ የገጸ ምድር ውሃ ፍሰት ይጠበቃል። ስለሆነም የሚመለከታቸው አካላት ተፋሰስ ተኮር የሆኑትን የሚከተሉትን የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳቦች ማከናወን ያስፈልጋል (ሠንጠረዥ 3)።

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች			
ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት የሚያገኙ ዞኖች	አዎንታዊ ተጽዕኖ	አሉታዊ ተጽዕኖ	የተሰጠ ምክረ ሃሳብ
ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ ዶሎ ፣ ነጎብ፣ ጃረር፣ ጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ ፣ ደቡብ አሞ ፣ የሲዳማ ሁሉም የክልሉ ዞኖች	➢ በጋ ተጠቃሚ በሆኑ ደጋማ አካባቢዎች ለተዘሩ ሰብሎች እድገት ➢ ለአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል ➢ የዝናብ ውሃን ለማሰባሰብና ለማጠራቀም	➢ የፀረ ሰብል ተባይ መከሰት ፤ ➢ በጥቂት ቦታዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት ዝቅተኛ መሆንና ➢ የእርጥበት ትነት መኖር	➢ የሚገኘዉን እርጥበት በአግባቡ መጠቀም ➢ ደጋማ አካባቢዎች ላይ ለተዘሩ ሰብሎች የአረም ማስወገድ ስራዎችን መስራት ➢ የዝናብ ውኃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል ➢ ለእንስሳት የግጦሽ ሣርን በአግባቡ መጠቀምና መጠበቅ፤
ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ የሚ ጠበቅባቸው ዞኖች			
ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት የሚያገኙ ዞኖች	አዎንታዊ ተጽዕኖ	አሉታዊ ተጽዕኖ	የተሰጠ ምክረ ሃሳብ
ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ኢሊአባቦራ፣ ጅማ ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ አርሲ ፣ ምዕራብ አርሲ፣ የሰሜን እና የምዕራብ ሸዋ፣ ባሌ ፣ የሰሜን፣ የመካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ የምስራቅ፣ ሰሜንና ምዕራብ	➢ የአፈር ውስጥ እርጥበት መኖር እንደ ሽንብራና ጓያ የመሳሰሉ በክረምቱ መጨረሻ ላይ ለተዘሩ የጥራጥሬ ሰብሎች ፍሪ ለማፍራት	➢ በደረሱ የመኸር ሰብሎች የሰብል ስብሰባ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ መኖር	➢ የደረሱ ሰብሎችን በሚኖሩት ደረቅ ሰሞናት የመሰብሰብና በአግባቡ የመከመር ተግባራትን ማከናወን ➢ አርሶ አደሮች የማሳ ጉብኝት በየጊዜው ማድረግ

ጎጃም፣ ዋግ ህምራ፣ ሰሜን ሸዋ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ ባህርዳር ዙሪያ ፣ አዊ ፣ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ፣ አኝዋክ፣ መዠርንግ፣ ኑዌር ፣ ኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ምዕራብ አሞ፣ ወላይታ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ ሲቲ፣ ፋፈን ፣ ኤረር ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ	➢ ለቋሚ ተክሎችና ለግጦሽ ሳር ዕድገት ➢ ዘግይተው ለተዘሩ ሰብሎች ፍሬ ለመሙላት ➢ በበጋ መስኖ ለሚከናውን የግብርና እንቅስቃሴ	➢ ከእርጥበትና ሙቀት የተነሳ የዋግ በሽታ መከሰት	➢ የጥራጥሬ ሰብሎች (ሽንብራ እና ጓያ) እድገትን መከታተል

ሠንጠረዥ 3 በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሀዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

መካከለኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት	አዎንታዊ ተጽዕኖ	አሉታዊ ተጽዕኖ	የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ
• ላይኛውና መካክለኛዉ በባሮ አኮቦ፣ • አሞ ጊቤ • መካክለኛዉና ታችኛዉ፣ በስምጥ ሸለቆ • ታችኛው ገናሌ ዳዋ	• የወንዞችና የግድቦች የውሃ መጠን መጨመር • ለመስኖና ለሃይል ማመንጫ የውሃ ክምችት መሻሻል • የገፀ ምድርና የከርሰ ምድር ውሃ ሀብት መጨመር	• የአፈር መሸርሸር • ከፍተኛ ትነት መኖር	• የጎርፍ መውረጃ ቦዮችን ማፅዳት • የዝናብ ውሃ ማሰባሰብና የግድቦችን የውሃ መጠን መከታተል
ከቀላል እስከ መካከለኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት	**አዎንታዊ ተጽዕኖ**	**አሉታዊ ተጽዕኖ**	**የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ**
• ታችኛው አሞ ጊቤ • ስምጥ ሸለቆ • ገናሌ ዳዋ፣ ዋቤ ሸበሌና አጋዴን • በጥቂት የአባይ እንዲሁም ላይኛው አዋሽ ተፋሰሶች ላይ	• የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል • የወንዞችና የትናንሽ የውሃ ማጠራቀሚያዎች መጠነኛ መሙላት • የአፈር እርጥበት መሻሻል	• የፍሳሽ መውረጃዎች መዘጋት	• የዝናብ ውሃ ከጣራና ከመሬት ወለል ማሰባሰብ • የፍሳሽ መውረጃዎችን ማፅዳት • ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በሚኖርባቸው ተፋሰሶች ወቅታዊ ትንበያዎችንና ቅድመማስጠንቀቂያ መከታተል።
ደረቅ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት	**አዎንታዊ ተጽዕኖ**	**አሉታዊ ተጽዕኖ**	**የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ**
• ተከዜና መረብ ጋሽ • አዋሽ፣ አፋር ዳናክል • ላይኛው ዋቤ ሸበሌ	• የጎርፍና የደለል ስጋት አለመኖር	• ከፍተኛ ትነት መኖር	• የሚገኘውን የውሃ ሀብት በአግባቡ መጠቀም